# ኦርኦቤዴል

የጥምቀት በዓል ልዩ ዕትም

ጥር 2015 ዓ.ም

## በቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤልና
## የጻድቁ አቡነ ጎርጎርዮስ ቤ/ክ ተስፋ ኢየሩሳሌም
## ሰንበት ት/ቤት



“በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥ በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።”

ቆላስይስ 2፥12

# ነገር ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል ዮሐ 1፡ 26

ስለ ሰው ልጆች ሁሉ መድኃኒት የሆነ የአምላካችንን መገለጥ እንዴት አድርገን መግለጥ ይቻለናል? እጅግ የሚያስጨንቅ ነውና። እርሱ ዓለምን ሁሉ ያስገኘ ሲሆን ዓለም የሌለችበት፣ የማይገኝ ልዑል ፤ በዓለም ሁሉ የሞላ ሲሆን ከዓለም ሁሉ የተሰወረ ነውና ማን ያውቀዋል ማን ያየዋል?! ገነትን ያበጃጀ መንግሥተ ሰማየትን ያዘጋጀ በየጊዜው አዲስ የሚባል እርሱ በመካከላችን ቆሞአል። መላእክት ሊያዩት የሚመኙት የነብያት ናፍቆት የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እግዚአብሔር በመካከላችን ቆሞአል።

ለተራመደው ለእያንዳንዱ አረማመድ ክብር ምስጋና ይግባውና ከዘመናት በፊት የነበረ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ እርሱ ሕጻናትን የሚያሳድግ ፣ ወራዙትን የሚያጎለምስ ፣ ጎልማሶችን የሚያገርም ሳለ እንደ ሰው ልማድ በጥቂት ጥቂት አድጎ በሠላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ቤተ ራባ ይጠመቅ ዘንድ ወደ ዮሐንስ ሄደ።ሄደ!... ያ መቶአለቃ ‹እኔም እኮ ገዢ ሰው ነኝ ወታደሮች አሉኝ አንዱን ሂድ ብለው ይሄዳል ና ብለው ይመጣል› ሉቃ 7፣8እንዳለው ከግርማቸው የተነሳ ብናያቸው ጸንተን መቆም የማይቻለን ግሩማን መላእክት ያሉትን በፍርሃት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው የሚያመሰግኑትን ሂዱ ብሎ የሚያዝ ፤ ከጽድቃቸው እና ከገድላቸው ብዛት ምድራዊያን ሳሉ ሰማያውያንን የተባሉ ቅዱሳንን ኑ ብሎ የሚጠራ አምላክ ትህትናን ሊያስተምረን፣ አብነት ሊሆነን ፣አንድነቱን ሦስትነቱን ሊገልጥልን ፣የዕዳ ደብዳቤያችንን ሊደመስስልን፣ ሥርዓትን ሊሠራልን በውኃ ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ ሄደ ።
ያስበን እና ያውቀን ዘንድ ምንም የሆንን እኛን ከወደደን ከጥልቅ ፍቅሩ የተነሳ በሕይወታችን ውስጥ በጸሎታችን ፊት በኅብረታችን መካከል እንደመጣ ፣እንደተገኘ፣ እንደቆመ አናውቀውና ቅድስት በምትሆን በጥምቀቱ ብርሃን በመካከላችን መቆሙን እንድናውቅ እና እንድናይ የልቦናችንን ዐይን ያብራልን! መንገዳችንን ሁሉ በትህትና እንድንሄድ መሄዱን ይስጠን!!



“በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥ በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።”
ቆላስይስ 2፥12

በቦሌ ደ/ም/ቅ/ሚካኤልና ጻ/አ/ ጎርጎርዮስ ቤ/ክ የ2014 ዓ.ም የከተራ በዓል አከባበር።



# ቃና ዘገሊላ



ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን በየዓመቱ የምታከብራቸው በዓላት መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን እነዚህም በሁለት ይከፈላሉ::

1.አዋድያት (Movable Feasts) እነዚህም መባጃ ሐመርን ተከትለው አንዳዴ ወደፊት አንዳዴ ወደ ኋላ በመመላለስ በየዓመቱ በተለያየ ቀንና ወር የሚከበሩ ናቸው በተለይ በዓቢይ ጾም የሚከበሩ ስቅለት ፣ትንሣኤ ሕማማት ፣ደብረ ዘይት ሆሣዕና መሰል በዓሎች ይገኙበታል::

2.አዋድያት ያልሆኑ (Immovable Feasts) የምንላቸው ሁል ጊዜ በአንድ ወር ውስጥ ባለ፣ በተወቀ ቀን ብቻ የሚውሉ ዘመን መለወጫ ፣ልደት ፣ጥምቀት ደብረ ታቦር ፣መስቀል ቃና ዘገሊላ ወ.ዘ.ተ ናቸው::

ለዛሬ ታዲያ በዚህ ጹሑፍ አዋድያት ካልሆኑት ውስጥ የቃና ዘገሊላ በዓልን እንመለከታለን::

ቃና ዘገሊላ ከስሙ እንደምንረዳው በገሊላ አውራጃ የምትገኝ የድሆችና የአህዛብ መንደር ስትሆን በዚህች ቦታ ጌታችን በዶኪማስ የሰርግ በዓል ላይ ተገኝቶ ከጥምቀት በኋላ ለዚያች ሀገር የመጀመሪያውን ተአምር አድርጓል። ይህም ጉዳይ ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያሉ ዓለም ዓቀፍ ጸሐፍያንን ትኩረት የሳበ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።

ከአራቱ ወንጌላውያን አንዱ የሆነው ዮሐንስም እንደንስር በጠሩ አይኖቹ እና እስከመጨረሻው አምዕሮን ወጥሮ በሚይዝ የአተራረክ ፍሰት በወንጌሉ ከ ምዕ2፥1-11 እንደዚህ አስቀምጦት ይገኛል።



በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች ፤ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት፦ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው። ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት።እናቱም ለአገልጋዮቹ፦ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው።

አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር፥ እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር።

ኢየሱስም፦ ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሏቸው። አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም። አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ፦ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።

ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።
ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፥ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ።የአይሁድ ፋሲካም ቀርቦ ነበር፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።

ይህ ጉዳይ ትኩረት እንዲስብ ካደረጉት ነገሮች አንዱ በገሊላ አውራጃ ነዋሪ እንዲሁም ለሙሽራው ዶኪማስ ቤተ ዘመድ የሆነችው ድንግል ማርያም ከልጇ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መገኘቱ ሲሆን ሌላኛው ጉዳይ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰርግቤቱ ያለቀውን የወይን ጠጅ በእናቱ ምልጃ የጋኖቹን ውኃ ወደወይን ጠጅ መለወጡ ነበር፡፡

<< ካታኮንብ>> (ግበበ ምድር) ከተገኙ ሃምሳ ሁለት ጥንታዊያን የዋሻ ውስጥ የግድግዳ ሥዕላት ከ አሥራ ሥድስት የሚበልጡት የቃና ዘገሊላ ተአምር የሚሳዩ መሆናቸው በዚያ የጭንቅ ዘመን የነበሩ የጥንት ክርስቲያኖች ስለዚህ ሰርግ ቤት ተአምር የነበራቸውን ትኩረት የሚሳይ ነው፡፡

ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የቃና ዘገሊላ ተአምር የተፈጸመበት ዕለት የካቲት 23 እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም የካቲት 23 ዕለት በዐቢይ ጾም ስለሚውል በዓሉን በደስታ ለማክበር እንዲሁም የውኃ በዓል ከዉሃ በዓል ጋር አንድ ለማድረግ ከጌታችን በዓለ ጥምቀት ማግሥት ጥር 12 ከ ቅዱስ ሚካኤል በዓል ጋር እንዲከበር አድርገዋል፡፡ ዮሐንስ ወንጌላዊም ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር የውሃን በዓል ከዉሃ ጋር በሚመስል መልኩ የቃናውን የሰርግ ቤት ታሪክ ከጌታ ጥምቀት ቀጥሎ መዘገቦት እናገኛለን፡፡

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልዩ ትኩረት ሰጥታ ከምታከብራቸው በዓላት አንዱ ከመሆኑም ባሻገር የቤተክርስቲኗ ሀብት በሆነው በቅኔ ታሪክ ውስጥም የሚታወስ ዕለት ነው፡፡ ከቅኔ መንገዶች አንዱ <<ጉባዔ ቃና>>ተብሎ ይጠራል እንደሚታወቀው የቅኔ ጀማሪ በኢትዮጵያ ቅዱስ ያሬድ ነው፡፡

ይህን የቅዱስ ያሬድ የቅኔ መንገድ እግዚአብሔር እንዲገልጥለት 1408 ዓ.ም ዮሐንስ ገብላዊ የተባለ ሊቅ ደብረ ታቦር በተባለ ተራራ ሱባዔ ይገባል፡፡ በዚህም ሱባዔ ምስጥር ከእነ ቤቱ ተገልጾለት ከቅዱስ ያሬድ አያይዞ ደርሷል፡፡ ይህንን ቅኔውን ለአባ ገብርኤል አስተማረ፤ አባ ወልደ ገብርኤል ለሠምረ አብ አስተማረ፤ ሠምረ አብ ቅኔውን ሲያስተምሩ በወቅቱ 1470 ዓ.ም ንጉሥ በዕደ ማርያም ነበር፡፡ ንጉሡም ቅኔውን በሰማ ጊዜ <<አንተ ከነ አባትህ ትለፈልፋለህ እንጂ ቅኔውን ከየት አገኘኸው>> ይለዋል መምህሩ ሠምረ አብም በትህትና ቃል እንዲ ካልክስ <<እንዲገልጥልን አብረን ለምን ሱባዔ አንገባም >>ንጉሡም እሺ ብለው ተያይዘው ሱባዔ ገቡ፡፡ እግዚአብሔርም ነገሩ ከእርሱ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ በሱባዔ ወቅት የንጉሡን ልብ ብሩህ አደረገለትና እንዲ ሲል ቅኔ ተናገረ፡፡

ድኅረ ተሰብረ አጽንዖ ለሰብእናነ ልሕኩት
ሰብሐዊ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት

ትርጉም:
ሸክላ (ሰብዕናችን)ከተሰበረ በኋላ ሸክላ ሰሪው ክርስቶስ በሐዲሲቱ ጥምቀት በውኃ አጸናው(ሠራው)

ይህን ቅኔ የመራበት (የተቀኘበት) ዕለት የቃና ዘገሊላ ዕለት በመሆኑም ስሙም ጉባኤ ቃና ተባለ፡፡ ቤተክርስቲያንም ጌታችን እጅግ ብዙ ተአምራት መካከል መርጣ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ (2፥1-11) በእናት እና ልጅ መካካል የተደረገውን ምልልስ በምዕራፍ 19 የሰው ልጅ ድኅነትን ሰማያዊ ክብር ጥልቅ ምስጢር መሆኑን ተረድታ ከጌታችን ንዑስ ባዕላት አንዱ አድርጋ ታከብረዋለች፡፡

